

## 35-2

# ከስርቆት ጠባይ እንሸሽ

**2) የአሥራት ሥርቆት**

ከአሥራት ስርቆት ነጻ የሚሆኑ እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው። አሥራታቸውን በትክክል የሚከፍሉ አሜሪካውያን ክርስትያኖች ከመቶ አምስት (5%) አይበልጡም ይባላል። በኢትዮጵያውያን አማኞች መካከልስ አሥራቱን በቀጥታ የሚከፍል ስንት ይሆን? በማንኛውም አገር የሚኖር ለመግሥት ቀረጥ ሳይከፍል የሚኖር የለም። በልዩ ልዩ መንገድ ሳይከፍል ቢቀርና ሌብነቱ ቢደርስበት ተከሶ ይፈረድበታል። አንድ አሜሪካዊ ሰባኪ ለመንግሥት መክፈል የሚገባውን ባለመክፈሉና የድርጅትን ገንዘብ ያለአግባብ በመጠቀሙ 45 ዓመት ተፈርዶበት እንደታሠረ ብዙዎቻችን እናውቃለን። ማንኛውም አማኝ ከሚያገኘው ገቢ ወይንም ደሞዝ ከመቶ አሥሩ (10%) የእግዚአብሔር ነው። ለምሳሌ በሳምንት 500 ብር ገቢ ያለው ሰው ሃምሣው ብር የእርሱ አይደለም። እርግጥ ነው የገንዘቡን ብዛት ሲያስበው ሊያጓጓው ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ ይሄ ገንዘብ የእግዚአብሔር እንጂ የራሳችን ስላልሆነ ከዚያ ገንዘብ መጠቀም የእግዚአብሔርን ገንዘብ መሥረቅ ይሆናል። ቤት ተከራይተን ቤቱን ለአከራየን ሰው ገንዘብ በቂ ቢኖረንም ባይኖረንም የቤቱን ኪራይ ሳንከፍል መኖር እንደማንችል ስለምናውቅ በግድ ከገቢያችን ቆርጠን ድርሻውን እንሰጣለን። ልክ እንደዚሁ ገንዘብ ቢያንሰንም ሌሎች ያልጠበቅናቸው ችግሮች ቢደርሱብንም የግድ አሥራታችን ተቀንሶ ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ድርሻ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። የእኛ ገንዘብ ስላልሆነ ልናዝበት ጨርሶ አንችልም። መዝገብ ይዞ "አልከፈልክም" ብሎ የሚቆጣጠረን ስለሌለ ብዙዎቻችን የእግዚአብሔር ገንዘብ ሌሎች ሆነናል። ይህንን ዓይንቱን ስርቆት ብዙዎቻችን ስለተለማመድነው ህሊናችን አይቆረቁረንም፤ በዚህ ምክንያትም ኃጢአት መስሎ አይታየንም። እንደ ምድራዊ ቀረጥ አስከፋዮች እግዚአብሔርም ቢያጋልጠን ኖሮ ስንቶቻችን የእግዚአብሔርን ገንዘብ በመስረቃችን ወህኒ ቤት በበሰበስን ነበር።

ከእግዚአብሔር የሠረቁ ፍርድን እንጂ በረከት የተቀበሉ ሰዎች አላየንም። ሐናንያና ሚስቱ ሳጺራ ከእግዚአብሔር ሊሠርቁ ሲሞክሩ ወዲያው በጴጥሮስ ፊት ወድቀው እንደ ሞቱ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ጴጥሮስ ሐናንያን "ሐናንያ ሆይ! በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንድትዋሽና ከመሬቱም ሽያጭ ከፊሉን እንድታስቀር ያደርገህ ሰይጣን ስለምን ወደ ልብህ ገባ? ሳትሸጠው በፊት መሬቱ የአንተ አልነበረምን? ከሸጥከውስ በኋላ ገንዘቡ የአንተ አልነበረም? ታዲያ ይህን ነገር ስለምን በልብህ አሰብህ? የዋሸኸው በእግዚአብሔር ላይ ነው እንጂ በሰው ላይ አይደለም" አለው (የሐዋ. 5፥3-4)። የእግዚአብሔርን ገንዘብ የምንሰርቀውን ሰዎች፥ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይለናል። "ሰው እግዚአብሔርን በማታለል መስረቅ ይገባዋልን? በእርግጥ አይገባውም፥ እናንተ ግን እኔን በማታለል ትሰርቁኛላችሁ፤ እናንተም ለመሆኑ የሰርቅንህ ነገር ምንድን ነው? ብላችኋል፤ የሰረቃችሁኝማ የዐሥራቱንና የመባውን ገቢ በመውሰድ፥ እናንተ የእሥራኤል ሕዝብ ዐሥራቴንና መባዬን በመስረቃችሁ የተረገማችሁ ሆናችኋል" ይላል (ትንቢተ ሚልክያስ 3፥8-9)።

የእግዚአብሔር ሰዎች አሥራታችንን ከእግዚአብሔር ባንሰርቅ ኖሮ ወይንም በታማኝነት ሁላችንም አሥራታችንን ብንከፍል ኖሮ ቤተ ክርስትያንም ሆነ መንፈሳዊ ድርጅቶች ገንዘብ በማጣት አገልግሎታቸው ወደ ኋላ ባልተጎተተም ነበር። ከሕዝብ የእግዚአብሔርን ገንዘብ ወይንም አሥራት የሚሰበስቡ አገልጋዮች የሰበሰቡትን ገንዘብ በአግባቡ መጠቀም ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። ተጠያቂነታቸው ከሰው ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔርም ጭምር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ አማኞች አሥራታቸው የእግዚአብሔር እንጂ የእነርሱ አለመሆኑን ዘንግተው የእግዚአብሔርን ገንዘብ እንደ ማስፈራሪያ ሊጠቀሙበት ይሞክራሉ። የአሥራታቸው ተቀባይ በሆነው ሰው ላይ በተለያየ ምክንያት ካኮረፉ፥ አሥራታቸውን መስጠት ያቆማሉ። እውነተኛ ጥሪ ኖሮት የሚያገለግል ማንኛውም አገልጋይ የአገልግሎት ሸክም ተሰምቶት ያገለግላል እንጂ የዚያ ሰው አሥራት እንዳይቀርበት ጎንበስ ቀና ብሎ እጅ ይነሳል ብዬ አላምንም። ያንን ሰው የጠራው አምላክ ለኑሮው የሚያስፈልገውን መስጠት ኃላፊነት እንዳለበት አምናለሁ።

## 3) የጊዜ ስርቆት

ብዙ “የጊዜ” ሌቦች አለን። የእኛ የኢትዮጵያውያን ችግር ግን ጊዜ ገንዘብ መሆኑን ስለማንረዳ በዚህ አንጻር ሌብነታችን አይታየንም። በአሜሪካን አገር በተለያየ ምክንያት ሠርተኞች ብዙ የሥራ ሰዓቶችን ይሠርቃሉ። ሰዓት አሳልፎ በመግባት ለምሳ ከተፈቀደው በላይ ሰዓት መውሰድ ሰዓቱ ሳይደርስ ከሥራ መውጣት ሳይታመሙ “ታምሜአለሁ” ብሎ ከሥራ መቅረት ብዙ የሥራ ጊዜ ይባክናል። ይህን በመሰለ ሁኔታ የሚባክነው ሰዓት በገንዘብ ተተምኖ በዓመት ከመቶ ሃምሳ እስከ ሦስት መቶ ሃምሳ ቢሊዮን ብር ($150-350 billion) እንደሚሆን ተረጋግጧል። ለምሳሌ ጄኔራል ሞተር ኩባንያ (General Motor) በዓመት ዘጠኝ ከመቶ (9%) የሥራ ቀናት ያለምክንያት ሠራተኞች እየቀሩ ይባክናል። ይህም ጄኔራል ሞተርን በአመት አንድ ቢሊዮን ብር ($1 billion) ይጠይቀዋል። በአሜሪካ ውስጥ በአንድ ቀን ያለ አጥጋቢ ምክንያት ከአንድ ሚሊዮን ሠራተኞች በላይ ከሥራቸው እንደሚቀሩ ታውቋል።

የአማኞችስ ይዞታ በዚህ አንጻር ከአለማውያኖች በምን ይህል ይለያል? በአሜሪካ ውስጥ አንድ ጊዜ በአንድ አካባቢ በተደረገው ጥናት መሠረት ሰላሳ ከመቶ (37%) ዓለማውያን ሳይታመሙ ታመናል ብለው ሲቀሩ፥ ሃያ ሰባት ከመቶ (27%) አማኞች ደግሞ ሳይታመሙ ታመናል ብለው እንደሚቀሩ ተረጋግጧል። ዓለም ከእኛ ከአማኞች ብዙ ይጠብቃል። ይሁን እንጂ ከዓለማውያኖች እምብዛም የተለየ አቋም ስለሌለን ለብዙዎች ጥያቄ ፈጥሮባቸዋል። እግዚአብሔር እኛን አማኞችን በጨለማ ዓለም ውስጥ ብርሃን (ምሳሌዎች) እንድንሆን ያቆመን በመሆናችን ሕይወታችን ጉልህ ሆኖ እንዲታይ እራሳችንን ማቅረብ አለብን።

በስንፍና ምክንያት ክርስትያኖች ከአሠሪዎቻቸው የጊዜ ሌቦች መሆን የለባቸውም። እግዚአብሔር ስንፍናን ይጠላል። ስለ ስንፍናም ብዙ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተጠቅሷል። “በሥራህ ትጉህ መሆን ክብርን ያስገኛል፤ ሰነፍ መሆን ግን ተገዥ ያደርጋል” (ምሳሌ 12፥24)። “ሰነፍ ብትሆን ችግር በመንገድህ እንደ እሾህ አጥር ይሆን ብሃል” (ምሳሌ 15፥19)። “ያለ ሥራ መቀመጥ እንቅልፍን ያስከትላል፤ ስለዚህ ሰነፍ ሰው ረሀብተኛ ይሆናል” (ምሳሌ 19፥15)። “አንዳንድ ሰዎች በጣም ሰንፎች ናቸው፤ ሌላው ቀርቶ በወጥ ያጠቀሱትን እንጀራ መጉረስ ይታክታቸዋል” (ምሳሌ 19፥24)። “መሥራት የማይፈልግ ሰነፍ ሰው ራሱን የገደለ ያህል ይቆጠራል” (ምሳሌ 21፥25)። “ሰነፍ ውጭ የወጣሁ እንደሆነ አንበሳ ያገኘኛል በማለት ከቤቱ አይወጣም” (ምሳሌ 22፥13) ይላል። ሰዓት የምናሳልፍ፣ ሳንታመም ታመናል የምንል፣ ዘመድ ሳይሞትብን ዘመድ ሞቶብን ብለን የሥራ ሰዓታችንን የምንሰርቅ የሰዓት ሌቦች መሆናችንን እኛ አማኞች እንገነዘብ ይሆን? ይህንን የምናደርግ ከሆነ ከዓለማውያን በምን እንለያለን?

## 4) በመ/ቤት ንብረት መገልገል ሌብነት ይሆን?

ለብዙዎቻችን ሥርቆት ማለት፥ የሌላውን ሰው ንብረት ሳንታይ የወሰድን እንደሆነ ብቻ ነው። በመሥሪያ ቤት ገንዘብ ወዳጅን መጋበዝና ዘመድ ለማፍራት ማስተናገድ ሌብነት አይሆንም? ለሥራ ጉዳይ ይህንና ያንን አወጣሁ ብሎ ትክክል ያልሆነ የወጪ ዝርዝር ማቅረብስ ስርቆት አይባልም? የመሥሪያ ቤት ዕቃ ለምሳሌ ደብተር ወረቀት ሌሎችንም እነዚህን የመሳሰሉትን ከመሥሪያ ቤት አውጥቶ መጠቀምስ ስርቆት አይሆንም? ከላይ ለጠቀስናቸው ጥያቄዎች መልስ መስጠት ይህን ያህል ያዳግተናል ብዬ አላምንም። በመሥሪያ ቤት ንብረት ያለፈቃድ መገልግል ሌብነት ከሆነ ክርስትያኖች በዚህ ላይ ምን ዓይነት አቋምና ምስክርነት ይኖራቸው ይሆን? በኢትዮጵያውያን ክርስትያኖች መካከል ምንም የተደረገ ጥናት ስለሌለ እንዲህ ነው ብለን መናገር አንችልም። ሁላችንም የግል ሕይወታችንን ስንመረምር፥ ምን ያህሎቻችን አውቀንም ሆነ ሳናውቅ የመሥሪያ ቤታችንን ንብረት መሥረቅ አለ መሥረቃችንን ማወቅ እንችላለን። በአሜሪካውያን ክርስትያኖች መካከል ግን ጥናት ተደርጎ አርባ ሦስት ከመቶ (43%) ክርስትያኖች ያልሆኑ ሠራተኞች የመሥሪያ ቤታቸውን ዕቃ እቤታቸው ወስደው ለግል ጉዳያቸው ሲጠቀሙብት ክርስትያኖች ነን የሚሉት ደግሞ ሰላሳ ሰባት (37%) የመሥሪያ ቤታቸውን ዕቃ ወስደው ለግላቸው መጠቀሚያ እንደሚያደርጉት ተረጋግጦአል። ይሄም የእኛን የክርስትያኖችን ምስክርነት ያበላሻል፤ ጌታንም አያስከብርም።

## 5) ልዩ ልዩ ዓይነት ስርቆት

በማወቅም ሆነ ወይንም ይህን ያህል ትልቅ ኃጢአት አይደለም በማለት በሕይወታቸው ትክክል ያልሆነ ነገር የሚለማመዱ አንዳንድ ክርስትያኖች እንደሚኖሩ ግልጽ ነው። እኛ ክርስትያኖች ምስክርነታችን በዓለማውያን ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው “ያለነቀፋ መኖር” ግዴታችን ነው። ከዚህ ቀጥሎ ሊያስነቅፉንና ምስክርነታችንን ሊያበላሹ ይችላሉ ብለን የምንላቸውን አንዳንድ “ስርቆት” ነው ብለን የምናምንባቸውን ሀሳቦች ለማስፈር ሞክረናል።

ሀ) የቴሌፎን ስርቆት፥ ብዙ መሥሪያ ቤቶች ለቴሌፎን ብዙ ወጪ ያወጣሉ። የወጪው ምክንያት አብዛኛውን ሠራተኞች የመሥሪያ ቤቱን ቴሌፎን ለግል ጉዳያቸው በመጠቀማቸው ምክንያት ነው። ይህን የቴሌፎን ስርቆት ለመቆጣጠር ብዙ መሥሪያ ቤቶች ልዩ ዓይነት መሣሪያ እየፈጠሩ ነው። በአሜሪካ ውስጥ አሥራ ሰባት ከመቶ (17%) የሚሆኑ ዓለማውያን የመሥሪያ ቤታቸውን የሩቅ ጥሪ ቴሌፎን ለግል ጉዳያቸው ሲጠቀሙ፥ አሥራ ሦስት ከመቶ (13%) የሚሆኑ አማኞች ለግል ጉዳያቸው የመሥሪያ ቤታቸውን ስልክ እንደሚጠቀሙ ተረጋግጧል። ክርስትያኖችስ ሆነን "በቴሌፎን ስርቆት" እንታማ ይሆን? እኛ ለግል ጉዳያችን በምንደውለው ስልክ መሥሪያ ቤቱን እናሰከፍል ይሆን? እንግዲህ ህሊናችንን እንመርምር። ዕቃ ወይንም ገንዘብ ብቻ ሳይሆን "የቴሌፎን ስርቆትም" አለና እንጠንቀቅ። ያወቅነውን በሥራ ላይ እናውል እንጂ ማወቁ ብቻ አይጠቅመንም።

ለ) ጉልበታቸውን የሚሠርቁ፥ ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞች በሥራ ሰዓት ጊዜያቸውና ጉልበታቸው የቀጣሪያቸው ሀብት ነው። ደሞዝ የሚከፈላቸው ጉልበታቸውን ወይንም አገልግሎታቸውን ሸጠው ነው። ታዲያ ደሞዝ እየተቀበሉ ግን የሚገባቸውን ሥራ በመሥራት ፈንታ እየለገሙ ሥራ ቢጎትቱ "ሌብነት" አይሆንም?

ሐ) የመንግሥት ቀረጥ በህቅ የማይከፍሉ፥ በተለይ አሜሪካን አገር የሚኖሩ የመንግሥት ቀረጥ ተገቢውን ሂሳብ ላለመክፈል ሲሉ ትክክለኛ ገቢያቸውን የሚደብቁ ያላወጡትን ወጪ አወጣን የሚሉ ብዙዎች ናቸው። አማኞችስ በዚህ ዓይነት ዘዴ ቀርጥ እንዳንከፍል መሸሽ "ስርቆት" ሆኖ ይታየን ይሆን? ወይንስ ሁሉም የሚያደርገው ስለሆነ እኔም አደርገዋለሁ ብለን "በስርቆት ልምምዳችን" እንቀጥል ይሆን?

መ) ያለአግባብ የኢንሹራንስ ካሣ የሚቀብሉ፥ በመኪና አደጋ ሳይጎዱ ተጎዳን ሳይታመሙ ታመምን ማለት በአሜሪካ አገር የተለመደ የንግድ ዘዴ ሆኗል። ክርስትያኖችስ በዚህ ዓይነት አቋራጭ መንገድ ለመክበር የሚፈልጉ ይኖሩ ይሆን? ያላወቅን እንደ ሆነ ይሄም "ስርቆት" ነው።

ሠ) የጽሁፍ (የስብከት) ስርቆት፥ የሰው ጽሑፍ እንደራሳቸው አድርገው የሚጽፉ ሌላው የሰበከውን ስብከት እንዳለ ገልብጠው እንደ ራሳቸው ስብከት የሚያቀርቡ አሉ። የሌሎችን ጹሁፍና ስብከት አንጠቀምም ማለት አይደለም። ስንጠቀም ጸሀፊው ማን እንደሆነ ወይንም ሰባኪው ማን እንደሆነ መግለጽ አለብን። ነገሩ ቀላል ይመስላል እንጂ ይሄም "ስርቆት" ነው።

"ኃጢአት" ሥንሠራ ለምን አይሰማንም? ኃጢአት ብዙ ጊዜ ደጋግመን ሥንሠራ፥ ህሊናችን የደነዘዘ ይሆናል። በዚህ ምክንያት ምንም አይቆረቁረንም። አንዳንዴ "በጸጋው ነው የዳናችሁት እንደ ልባችሁ ኃጢአት ሥሩ" ተብለን የፈቃድ ወረቀት የተሰጠን እንመስላለን። ጥቃቅን ሥርቆት ከለመድን ሳናውቀው ትላልቁ ውስጥ እንገባለን። በሌላ በኩል ደግሞ ህሊናችን እንዳይቆረቁረን የራሳችን የሆነ የመከላከያ ዘዴ (Defense mechanism) ፈጥረናል። አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል፥ "ይህን ያህል ፍጹም አይደለሁም" "ጥቃቅኑን ሁሉ ኃጢአት እያልኩ እራሴን አላስጨንቅም" "ክርስትያኑ ሁሉ ያደርገዋል፤ ማንም ከዚህ ንጹህ የለም" "ማንም አያወቅም" "እንዲህ ካላደርግሁማ በትክክለኛው መኖር አልችልም" "በጸጋ እንጂ፥ በሥራ አልድንም" "ከሌሎች ሠራተኞች ልዩ ሆኜ ብገኝ፥ በገዛ እራሴ ጠላት አተርፋለሁ"፤ በማለት ሳይቆረቁረን በኃጢአት ውስጥ እንኖራለን።

.........................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**